# «የወያኔ ምስጢራዊ መረጃ፤ ጆሮ ያለው ይስማ» በርእሱ እንዳትሸወዱ

# (ተክለ ሚካኤል አበበ)

February 8, 2015

ከዝግጅት ክፍል

አቶ ተክለ ሚካኤል አበበ ከዚህ በታች ያለውን ጽሁፍ በኢትዮፍሪደም ድሕረ ገጽ እንዲወጣለት ሲጠይቀን ጽሁፉን በጥሞና ተመለከትነው:: ጽሁፉ ከዚህ በፊት ሻርለት
ኖርዝ ካሮላይና ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተቀሰቀሰው ትርምስ ሳቢያ ተፈጽመዋል ስለተባሉት የሙብት ጥሰቶች በአቶ ተክለ ጊዮርጊስ (ከአትላንታ) ለተጻፈ ጽሁፍ መልስ ነው:: አቶ ተክሌ ከካናዳ ተስፈንጥሮ ሻርለት ውስጥ ለምን ዘልሎ ገባ (መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ) የሚለውን የአንድ ሚሊዮን ብር ጥያቄ ወደ ጎን ትተን ወደ ጽሁፉ እንመለስ::
የአቶ ተክሌ ጽሁፍ ባጠቃላይ ትንሽ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት የጎደለውና በአላስፈላጊ እንቶ ፈንቶ የተሞላ ሆኖ አገኘነው:: አቶ ተክሌ በማስረጃ አስደግፎ አቶ ተክለ ጊዮርጊስ ከአትላንታ ለጻፈው ጽሁፍ መልስ መስጠት ሲገባው የግንዛቤ ድህነትን ያዘለ በሚመስል ጅምላ አመለካከት መደምደምያውን ሰጥቶአል:: በዚህ ዱልዱም ድምዳሜው ላይ የዝግጅት ክፍሉንም ከአትላንታው ጸሃፊ ጋር አንድ ለማድረግ ሲዳዳው ይታያል:: በተጨማሪም አቶ ተክሌ አንድ ሌላ ሃቅ ሆን ብሎ ለመደበቅ ሲውተረተር መገንዘብ ይቻላል:: የአቶ ተክለ ጊዮርጊስ ጽሁፍ በኢትዮፍሪደም ድህረ ገጽ ላይ ብቻ እንደወጣ ለማስመሰል ሞክሯል:: እውነቱ ግን የአቶ ተክለ ጊዮርጊስ ጽሁፍ በኢካዴፍ በቋጠሮና በአሲምባ ድሕረ ገጾች ላይ ወጥቶአል:: ሌሎችን ትቶ በኢትዮፍሪደም ድህረ ገጽ ላይ ብቻ ለምን አቶ ተክሌ አተኮረ የሚለው ሁለተኛው የአንድ ሚሊዮን ደለር ጥያቄ ነው::
ከአትላንታ አቶ ተክለ ጊዮርጊስ የጻፉትን ጽሁፍ ኢትዮፍሪደም ድሕረ ገጽ የተቀበለውና ያወጣው በቤተ ክርስቲያን ትርምስ ውስጥ የመግባት አባዜ ስለያዘው አይደለም:: እንዲያውም በአሁኑ ጊዜ አሳፋሪ ደረጃ ላይ የደረሰውን ይህን የቤተክርሲትያን አምባጓሮ ጉዳይ ዝግጅቱ ክፍል በከፍተኛ ሃዘንና ትዝብት ነው የሚመለከተው:: በተቻለ መጠን እነዚህን ነውረኛ ውዝግቦችን ላለማስተናገድ ይሻል:: ነገር ግን በዚህ በሻርለት የቤተ ክርስቲያን ግብግብ ውስጥ በአንድ የዋልድባ መነኩሴ ላይ ከአሳፋሪም በላይ አሳፋሪ የሆነ ከቤተ ክርስቲያን ባሻገር የዘለቀ ድንበር ዘለል የሙብት ጥሰት መፈጸሙን ስላመነበት ጽሁፉ እንዲወጣ በጊዜው ወስኖ ነበር::
በተጨማሪ ለዚህ መብት ጥሰት ዋነኛ ተጠያቂ ነው ተብሎ በአቶ ተክለ ጊዮርጊስ ስሙ የተጠቀሰው ግለ ሰብ ከወያኔ ጉጅሌ አፋኝ ቡድን ጋር የጥቅም ግንኙነት ፈጥሮአል (በስህተትም ይሁን ነገሩ ባልታወቀ ምክንያት) ተብሎ በተባባሪ በማስረጃ የተደገፈ ዶኩመንት በመያያዙ የአቶ ተክለ ጊዮርጊስን ጽሁፍ ለማውጣት ተገደናል:: ነገር ግን በአትላንታው ጸሃፊ የተወሰደውን ማለት ከላይ የተጠቀሰው ግለሰብ ወያኔያዊ ርምጃ ነው የወሰደው የሚለውን ድምዳሜ የኢትዮፍሪደም ድህረ ገጽ በአሁኑ ሰዓት አይጋራም:: ያ መደምደሚያ የደራሲውና የደራሲው ብቻ ነው:: መውደቅ መሳሳትና በገንዘብ መቸነፍ በሕይወት ውስጥ ያሉ ክስተቶች ናቸው:: ጥሩ ሰዎች መጥፎ ነገሮች ሊሰሩ ይችላሉ:: ምክንያታቸው ግን የረቀቀ ሴራ ለማጠንጠን ላይሆን ይችላል:: በዚህ ምክንያት ነው የዝግጅቱ ክፍል የግለሰቡን የፖለቲካ አቋም ጥያቄ ውስጥ ሳያስገባ ድርጊቱን ብቻ ያወገዘው:: ፍርዱን ለጊዜና ለአንባቢያን ትተናል::
ባጠቃላይ አቶ ተክለ ሚካኤል መልስ ሲሰጥ ለፍርዱና ለስድቡ ከመቸኮሉ በፊት በግልጽና በማያወላውል ሁኔታ ከላይ በተጠቀሱት ሁለት አበይት ነጥቦች ላይ ማተኮር በተገባው ነበር:: በአገር ወዳዱ የዋልድባ መነኩሴ ላይ ለተወሰደው ርምጃና ሰብአዊ መብት ጥሰት ፈጽሞአል የተባለው ግለሰብ ከህወሃት ጋር በመተባበር የመሬት መቀራመት ተግባር ተሳትፎአል ለሚሉት ክሶች ማለት ነው:: አቶ ተክሌ ሚዛናዊና በማስረጃ የተደገፈ

የመከላከያ መልስ መስጠት ሲኖርበት እጅግ በጣም በወረደ መልኩ ከወያኔ ባላነሰ ሁኔታ ዲያስፖራውን በማንቋሸሽና የጅምላ ጥላሸት በመቀባት ጭምር መልሷል:: ይህ በጣም የሚያሳዝን ነው:: ዲያስፖራ ስህተት አይሰራም ማለት አይደለም:: እንዲያውም ድክመቶችና ስህተቶች ቁጥራቸው ተበራክቶ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን በዲያስፖራ ውስጥ ቡዙዎቻችን የምንሸሸውን መስዋእትነትን እየከፈሉ ቤተሰባቸውን በድለው የግል ጥቅማቸውን ወደ ጎን ትተው ቀን ተለሊት የሚታገሉ አበበ ገላውን የመሰሉ ግን ስማቸው የማይታወቅና ያልተዘመረላቸው የኢትዮጵያ ብርቅ ልጆች አሉ:: በአንጻሩ ደግሞ ከመስዋእትነት ተግባር ራሳቸውን አግልለው ግን አልፎ አልፎ እንደመስቀል ወፍ ብቅ እያሉ አንዱን ከፍ አንዱን ዝቅ እያረጉ ፍርድ ሲሰጡና ሲሻቸው ደግሞ የእርግብ እንቁላል ፍርፍር ይቅረብልን ብለው የሚያስቸግሩን እንደ አቶ ተክሌን የመሳሰሉ ወንድሞችም ደግሞ መሃላችን አሉ:: በተለይ የአቶ ተክለ ሚካኤል ጉዳይ “የት ይደርሳል የተባለ ጥጃ ልኳንዳ ተገኘ” ሆነ መቅረቱ እጅግ ያሳዝናል:: ከጸሎት ሁሉ ዋናው “መጨረሻዬን አሳምርልኝ አምላኬ” ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም:: ይህን ጸሎት ስናስብ ደግሞ ልባችን በሃዘን ተሞልቶ ልደቱ አያሌውና ሌሎችም ትዝ ይሉናል::
የኢትዮፍሪደም ድህረ ገጽ አቶ ተክለ ሚካኤል አበበን ይህን ጽሁፉን አስተካክሎ እንደገና እንዲልክ ቢጠይቀው አሻፈረኝ ብሎ ይህማ ሴንሰርሽፕ ነው በማለት አመረረ:: እኔ የምለው ሁሉ ካልሆነ ሴንሰርሽፕ ነው የሚለው:: ዲሞክራሲ እውነት የሚመስላቸው ለእነሱ ሲጥማቸው ብቻ እንደሆነ የሚያምኑት ሰዎችን ዓይነት መሆኑ ነው:: ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ እንዳለችው የቤት እመቤት እኔ የምሻውን በምፈልገው መንገድ ብቻ የማያስተናግደኝ ዲሞክራሲ በአፍንጫዬ ይውጣ ነው ተክሌ የሚለው ::ፈረንጆቹ ናርሲስቲክ የሚሉት ዓይነት ባህርይ ነው:: ይህን ባህርይ የተላበሰ ሰው ስለ ደንብ ስለ ሥነ ሥርዓት ስለ ብቃትና ስለ ጥራት ብዙ አይደንቀውም:: እርሱ የሚያስበውና የሚያደርገው ሁልግዜ ትክክልና እንከን የማይገኝለት እንደሆነ ነው ከልቡ የሚያምነው:: መጠነኛ የመረጃ ክፍተት ሊኖርብኝ ይችላል ብሎ እንኳን አይጠረጥርም:: በዚህ ምክንያት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ውስጥ እንዲህ ዓይነቱ ባህርይ ግልገል አምባገነኖችን ሲፈለፍልና አብሮ በቡድን የመሥራትን ልማድ (Team Work) ሲያደናቅፍ ይታያል:: የፖለቲካ ድርጅቶች በየጊዜው እየተቋቋሙ በየጊዜው መፍረስ እንዲሁም የፖለቲካ ድርጅቶች አንድነት መፍጠር ያልቻሉበትም ዋናው ምክንያት ይህ ነው::አንድ ተሰላችተው ከትግሉ ጡረታ የወጡ የቀድሞ ታጋይ እንዳሉት አንዳንዶቻችን በኪሳችን ትንንሽ ዘውድ ይዘን የምንዞር ይመስላል:: ለምን ቢሉ አጋጣሚ ብናገኝ ለመንገሥ ብለው ተናገሩ አሉ:: አቶ ተክሌ በኪሱ ዘውድ ይዘው ከሚዞሩት አንዱ ይሆን?
አቶ ተክሌ ትንሽ የወረደና ቡዙዎችን ሊያስደነግጥ የሚችል መልስ የጻፈ ቢሆንም መልስ መስጠት መብቱ ነው::

ራሱን እንደ አንድ ፀረ -ወያኔ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ነኝ የሚለው አቶ ተክሌማንም ሰው የዲያስፖራ ኢንቨስተር እየተባለ ከገበሬዎችም ሆነ ከደሃ ነዋሪዎች ላይ በወያኔ በግፍ የተነጠቀ መሬት (ይህ በዝምድና በቤተሰብና በግል የመሬት ገበያ ላይ የሚገዛን መሬት አይመለከትም) ገዝቶ ቤት መሥራት ይችላል ብሎ ሲከራከር መስማት ቡዙዎቻችንን ሳያስገርም አይቀርም:: በይበልጥም ደግሞ በአንድ ወቅት የኢሳት ቲቪ ባልደረባ የነበረው አቶ ተክለ ሚካኤል አበበ በአደባባይ እንዲህ ሲሞግት መስማት በሕልሙ ነው ወይስ በውኑ ነው ያሰኛል:: “ወጣ ወጣና እንደ ሽምበቆ ተንከባለለ እንደሙቀጫ” ሳያሰኝም አይቀርም::
ለመልሱ ግን ተጠያቂው እርሱ ነው:: ከሙብት ጋር ተጠያቂነትም አብሮ ስለሚሄድ አቶ ተክለ ሚካኤል አበበ የጽሁፉን እንድምታ በተግባር ከሕዝብ እውነተኛውን ፍርድ እንደሚያገኝ ባለመጠራጠር የጥራት መመዘኛችንን ባይጠብቅም ጽሁፉን ያለምንም እርማት እንደወረደ አውጥተነዋል:: አሁንም እንደገና ፍርድ ለእናንተ::
አቶ ተክለ ጊዮርጊስ ከአትላንታ የጻፈውን ጽሁፍ ለማነጻጸር እንዲመች ይህን ሊንክ በመጫን ይመልከቱ::
የአቶ ተክለ ሚካኤልን ጽሁፍ ከዚህ በታች ይመልከቱ::

«የወያኔ ምስጢራዊ መረጃ፤ ጆሮ ያለው ይስማ» በርእሱ እንዳትሸወዱ
ተክለ ሚካኤል አበበ
February 8, 2015
1- ይሄ የኔ ርእስ አይደለም:: የዛሬ 15 ቀን ተክለጊዮርጊስ በተባሉ (የብእር ይሁን የምር ስም አይታወቅም) ሰው የተጻፈን ስም አጥፊ ጽሁፍ የለጠፈው ኢትዮፍሪደም ድረገጽ ወይም የጽሁፉ ደራሲ፤ የአንባቢን ትኩረት

ለመሳብ ይመስላል፤ የተጠቀሙበት የመግቢያ ሀይለቃል እንጂ፡፡ ጸሀፊው ለድረገጾች ያላቸውን ቅርበት በመጠቀም፤ እንዲሁም ወያኔ የተባለው ቃል ከተጠራ አንባቢ አያጣራም፤ ወይም ግለሰቡ ላይ ዘሎ ይረባረብበታል በሚልና፤ የስም ማጥፋቱ ሰለባ የሆኑት ሰው፤ ጨዋና እንዲህ ያለው እንከሰላንቲያ ውስጥ ገብተው አይመልሱም በሚል እሳቤ ይመስላል፤ ይሄንን ርእስ ተጠቅመዋል፡፡ በርግጥም ጸሀፊው አላማቸው በተወሰነ መልኩ ተሳክቶላቸው፤ የተሻለ ያስባሉ የምንላቸው ሰዎች ጭምር፤ ጽሁፉ ላይ የተነሰነሱትን ፎቶኮፒ አባሪዎች አይተው፤ ጸሀፊው በሚፈልገው መንገድ ሄደዋል፡፡ በዚህ ሰአት በዚህ ርእሰ-ጉዳይ ላይ መጻፍ፤ ብዙ አንገብጋቢ ባይሆንም፤ የንጹኀን ግለሰቦችን ክብር ለመጠበቅና፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተለመደ የመጣን አጉል ባህል ለመዋጋት ስል፤ ይህንን እጽፋለሁ፡፡




2- ነገሩን እንዲህ ነው፡፡ እጅጉ ገዳሙ (ሻለቃ) እና ገበየሁ ይገዙ (ዶ/ር) (ሁለቱም የፈጠራ ስሞች ናቸው) ነዋሪነታቸው በሻርለት፤ ሰሜን ካሮላይና ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ኢትዮጵያዊን፤ ባለፉት ጥቂት አመታት ኢትዮጵያን የተመለከት ክስተት ካለ ሌሎች አጋሮቻቸውን አስተባብረው ብዙ መቶ ኪሎሜትሮችን ነድተው ለመምጣት አያመነቱም፡፡ ለምሳሌ፤ የኢሳት ገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅት አለ ከተባለ፤ ከሌሎች ወዳጆቻቸው ጋር አትላንታ ድረስ ነድተው ሲመጡ ተመልክቻለሁ፡፡ የዋልድባ መታረስን/መፍረስን ከተትሎ ተቃውሞ አለ ሲባልም፤ ዋሽንግተን ዲሲ ድረስ ነድተው ሲመጡ አስታውሳለሁ፡፡ እነዚህ ሁለት ኢትዮጵያዊያን ኢትዮጵያን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ሁሉ፤ አብረው የሚሰለፉ የአንድ አካባቢ ነዋሪዎች ናቸው፡፡ ነበሩ፡፡

3- በቅርቡ ግን፤ የሻርለት ስላሴ ቤተክርስቲያን አባላትን የከፋፈለ ክስተት ተፈጠረ፡፡ የክፍፍሉ ዝርዝር አይገባኝም፡፡ ግን በሌሎች በብዙ ስፍራዎች ከሚከሰቱ ውስጣዊ አለመግባባቶች ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ብዙ ቦታ ብዙ ግዜ ተጽፎ እንዳያችሁት፤ በተለይ ቤተክርስቲያኖቻችን በውስጣዊ ክፍፍል ሲመቱና ሲታመሱ ከርመዋል፡፡ ቀደም ሲል፤ አብዛኛው ክፍፍል፤ የውጭ አገርና የአገር ውስጥ ሲኖዶስ፤ እንዲሁም ገለልተኛ በሚል ምክንያት ነበር፡፡ በዚህ ረገድ፤ የሻርለት ስላሴ ቤተክርስቲያን፤ ከስደተኛው ሲኖዶስ ሆኗል፡፡ ከዚህ ውሳኔ በኋላ የተቀሩትን ምእመናን የሚያጠናክር እንጂ የሚከፋፍል ነገር ሊፈጠር አይገባም ነበር፡፡ አለመታደል ሆኖ ግን፤ በሻርለትም ይሁን በሌሎች ስፍራዎች፤ ለምሳሌ በዲሲ ገብርኤል፤ በሲያትል ገብርኤል፤ በቫንኩቨር ማርያም፤ በጀርመንና በሌሎችም ስፍራዎች ጭምር፤ ቤተክርስቲያናት፤ ወደስደተኛው ሲኖዶስ መሆናቸው ከለየላቸውም በኋላ፤ ሌላ የመከፋፈልና የመካሰስ እንዲሁም የመከፋፈል ችግር ይስተዋልባቸዋል፡፡

4- የበለጠ የሚያበሳጨው ግን የመከፋፈሉ ችግር ሳይሆን፤ አንደኛው ወገን ሌላኛውን ወገን ለማሸነፍ የሚጠቀማቸው አግባብና ጤናማ ያልሆኑ ዘዴዎች ናቸው፡፡ ችግሩን ሲሆን ሲሆን በውይይት ያለበዚያም በፍርድቤት ለመፍታት መሞከር አንድ ነገር ነው፡፡ ገና ለገና በራስን ወገን ላይ ድል ለመቀዳጀትና፤ ማንም አሸናፊ ሆኖ የማይወጣበትን ግብግብ በጊዜያዊ ድል ለመወጣት በሚል፤ ያለበለዚም ባልበላው እጭረዋለሁ በሚል የዶሮ ስሌት፤ ስም ማጥፋት፤ በሀሰትና በፈጠራ ክስ ሰዎችን መወንጀልን እንደ ማጥቂያ መንገድ መጠቀም አግባብም፤ መንፈሳዊም፤ አዋጭም አይደለም፡፡ ያ መንገድ ቢያዋጣ፤ ኢህአፓ እስካሁን ስልጣን ይዞ ነበር፡፡ ግን አላዋጣም፡፡ ባለፈው ሁለት ሳምንት፤ በሻርለቱ ዲባቶ ሰለሞን ጉግሳ ላይ የተሰነዘረው የስም ማጥፋት የዚህ ውስጣዊ ሕጋዊ ችግርን በስምማትፋት የመፍታት ስልት አይነተኛ መገለጫ ነው፡፡

5- አቶ ተክለጊዮርጊስ (ምናለ እንደኔ ጊዮርጊስ የሚለውን ትተውት ተክለ ብቻ ቢሉ)፤ በዲባቶ ሰለሞን ላይ ያነሷቸው ክሶች ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው ኢትዮጵያ ቤት ለመስራት መሬት ወስደዋል፡፡ ሁለተኛ የዋልድባ መነኩሴ አባረሩ የሚል ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህን ያደረጉ ሰው፤ በውጭ የሚገኙ የሰብአዊ ሙብት ድርጅቶች ውስጥ በአባልነትም ይሁን በአመራር ላይ ከተቀመጡ፤ በኢህአዴግ ለስለላ የተቀመጡ ሰው ናቸው የሚል ክስ ነው፡፡ ይሄንን ክስ ይዘው ከለጠፉት አንዳንዶቹ፤ ለካንስ ዶሮዎቻችንን አደራ የሰጠነው ለቀበሮች ሲሉ ተረቱ፡፡ አገርቤት ቤት መስራትንም ከስስትና ከራስወዳድነት ጋር አገናኙት፡፡ እንዴት ያለ የሀሳብ ድህነት ነው ባካችሁ፡፡ እንዲህ እመልሳለሁ፡፡

6- ከቤት ስራ ጋር በተያያዘ፤ ሰው ገንዘብ ካለው፤ አገር ቤት፤ ቤት ቢገነባ በብዙ መልኩ ጠቃሚና

መበረታታት ያለበት ነገር ነው፡፡ አገራቱን፤ እንኩዋንስ እኛ፤ ማንም አረብና ህንድ እየሄደ እየተቀራመታት አይደለም እንዴ፡፡ አያት ቅድመአያታችን ባቆዩልን አገር ላይ ሄደን እንኩዋንስ ቤት፤ ምንስ ብንሰራ ክፋቱ ምን ላይ ነው፡፡ በውጭ ከምንገኝ ተቃዋሚዎች ዘመቻ ውስጥ ሁሉ የማይረባውና ስሜት የማይሰጠው፤ ለወያኔ ዶላር ስለሚያስገኝለት፤ በኢትዮጵያ አየር መንገድ አትጠቀሙና ቤት አትስሩ የሚለው ዘመቻ ነው፡፡ የምንቃወመው እኮ ስርአቱን እንጂ አገሪቱን አይደለም፡፡ ቤት መገንባትም ይሁን እንደኢትዮጵያ አየርመንገድ ያሉትን ድርጅቶች ቦይኮት ማድረግ ለትግሉ አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምን ሰው ያንን ማድረግ መብቱ ነው፡፡ ሌሎች በዚህ መስመር ያልተሰለፉትን ሁሉ ግን የስርአቱ ደጋፊዎች ወይም እንደአቶ ተክለጊዮርጊስ ጽሁፍ ርእስ ወያኔ አድርጎ መመልከት፤ ወይንም በውስጣችን በሕወሀት የተተከሉ ፍልፈሎች አድርጎ መሳል፤ የትግል ሳይሆን የድንቁርና መገለጫ ነው፡፡

7- ከስራ ከተሰናበቱት መነኩሴ ጋር በተያያዘም፤ ከዶ/ሩም ዘንድ ይሁን ከአካባቢው ካሉ ሰዎች ዘንድ ማጣራት እንደቻልኩት፤ አንደኛ ውሳኔው የተወሰነው በቤተክርስቲያኑ ሰበካ ጉባኤ ሲሆን፤ ዶ/ሩም ይሄንን ውሳኔ የማስፈጸም ግዴታ አለባቸውና ያንን ካስፈጸሙ፤ እርምጃው ስህተት ነው የሚል ወገን ካለ፤ መውቀስ ያለበት እሳቸውን ብቻ ሳይሆን፤ ሰበካ ጉባኤውን በሙሉ ነው፡፡ ሁለተኛ፤ የኛ ካህናት መረዳት ያለባቸው ነገር ቢኖር፤ ቤተክርስቲያናት በዚህ አገር ህግ የተመዘገቡ ድርጅቶች በመሆናቸው፤ ካህናቱም የቤተክርስቲኒቷ ተቀጣሪ ሰራተኞች እንደመሆናቸው መጠን፤ የቀጠራቸው አካል በምክንያትም ይሁን ያለምክንያት በፈለገው ሰዓት ሊያባርራቸው ወይም ሊያሰናብታቸው ይችላል፡፡ ከመነኩሴው ጋር በተያያዘ፤ የኢትዮፍሪደም ድረገጽ ባለሟል አቶ ኪሩቤል፤ መነኩሴው መባረራቸውን፤ የኢሚግሬሽን ጉዳያቸው መቋረጡን፤ እንዲሁም ቤተክርስቲያን ገብተው እንዳያገለግሉም መደረጋቸውን እንደለየለት ጭካኔ አድርጎ የወሰደው ነገርም ብዙ አያስኬድም፡፡

8- ካህኑ ይሄን አጥፍተዋል ይሄን አላጠፉም ብሎ መከራከር የዚህ ጽሁፍ ዓላማ አይደለም፡፡ ነግር ግን፤ ሰበካ ጉባኤው፤ መነኩሴው አብረዋቸው ሊዘልቁ የሚችሉ ካልመሰላቸው፤ በጊዜ ከስራ ቢያሰናብቷቸው፤ ያንንም ተከትሎ፤ የጀመሩላቸው የኢሚግሬሽን ማመልከቻ ካለ፤ ሰበካ ጉባኤው ራሱን ከዚያ ሂደት ቢያገል፤ ምክንታዊ ነው፡፡ እንዲሁም፤ የሳቸው ወደቤተክርስቲያን መግባት ሊያስነሳው የሚችለው ችግር ካለ፤ ያንን ለማስቀረት ሲባል በሰበካ ጉባኤው ጠያቂነት ፖሊስ ወደውስጥ እንዳይገቡ ከከለከላቸውም ለሁሉም ወገን እንደጥንቃቄ እንጂ እንደጭካኔ መወሰድ የለበትም፡፡ እንጂ፤ መነኩሴ ከዋልድባ መጣ ተብሎ፤ እንዲሁም መነኩሴ ኢህአዴግን የሚያወግዝ መፈክር አሰማ ተብሎ አይነካ የሚለው አባባል ብዙ አያስኬድም፡፡ ከመነኩሴው ጋር በተያያዘ የተፈጠረው ችግር ሲከሰት እንደሰማሁት ከሆነ፤ የመነኩሴውን መሰናበት ጉዳይ ጎንደሬ ከመሆናቸው ጋር አገናኝተው የአካባቢያዊ ጸብ ቅርጽ ሊያሲዙት የሞከሩም ሁሉ ነበሩ፡፡ ደግነቱ፤ በዚህ በሻርለት በተፈጠረው ችግር ውስጥ የጳጳሳቱም/ሲኖዶሱም እጅ ስላለበትና፤ በዚህ በስደቱ ሲኖዶስ ውስጥ በሚፈጠረው ሽኩቻ ውስጥ በሁለቱም ወገን ያሉት በአብዛኛው የጎንደር ሰዎች በመሆናቸው ችግሩ በዚህ ረገድ ገፍቶ አልሄደም፡፡

9- ዲባቶ ሰለሞን፤ የሰሜን አሜሪካውን የተቃውሞ እንቅስቃሴ በሚሾፍሩት ፊታውራሪዎቻችን ዘንድ የታወቁ ሰው ናቸው፡፡ ለምሳሌ፤ ባለፈው አመት በሳኡዲ በኢትዮጵያዊያን ላይ የደረሰውን በደል ተከትሎ የተቋቋመው ግሎባል አሊያንስ የተሰኘ ድርጅት አመራር አባልም ነበሩ፡፡ ግሎባል አሊያንስም፤ ዲባቶ ሰለሞን ላይ ይሄ ሁሉ ውርጂብኝ ሲወርድ አለማስተባበሉ፤ እንዲያውም እንደተባለው ካሉበት ሀላፊነት እንዲወርዱ ጫና አድርጎም ከሆነ፤ የተቃውሞ ስብስባችን ፍልስፍና ግልብና ከኢህአዴግ ያልተሻለ መሆኑን የሚያሳይ ጥሩ ማስረጃ ነው፡፡ ቢያንስ በድርጅቱ ላይ ጥያቄ ይፈጥራል፡፡ ማህተም ያለበት ደብዳቤና የቤት ስራ ማህበር አባላትን የያዘ ፎቶኮፒ ወረቀት የተነሰነሰበት ጽሁፍ ባየን ቁጥር ከላይ በርእሱ እንደተጠቀሰው ሾልኮ የወጣና የተደበቀ በአገር ላይ የሚሰራ ሴራ አድርገን ወደመመንዘር ካዘነበልን፤ ከመካከላችን ከዚህ ክስ የሚተርፍ አንዳችም ሰው የለም፡፡ እኔ በምሳተፍበትና ይሄንን የማይረባ ጽሁፍ ባነበብኩበት የቡድን ኢሜል ስብስብ ውስጥ ካሉት የግሎባል አሊያንስ ወገን በኩል አንዳችም ሰው ማስተባበያ አለመሰማቱ፤ አሞኛል፡፡ አበበ ገላው፤ በግሉ ስለዲባቶ ሰለሞን የሰጠው ጥሩ ምስክርነት እንደተጠበቀ ሆኖ፡፡

10- የዲባቶ ሰለሞንን ሁኔታ ቢያንስ ላለፉት አራት አመታት ተከታትያለሁ፡፡ ከቤተክርስቲያናቸው ጋር በተያያዘ በወሰዱት እርምጃ የማይስማማ ይኖራል፡፡ በምንም መልኩ ግን የፖለቲካ ስብእናቸውን ጥያቄ ውስጥ የሚከትና ከኢህአዴግ ጋር የሚቀላቅላቸውም ምንም አይነት ፍንጭ የለም፡፡ ዲባቶ ሰለሞን፤ በ 2010 ኢሳት

ሲመሰረት፤ ለኢሳት ገንዘብ በማሰባሰብ ረገድ ከመጀመሪያው ተርታ የተሰለፉ ናቸው፡፡ ለኢሳት በመደበኛነት ከሚሰጡት ርዳታ ጎን፤ ኢሳት የሙቶም ያምስትሙቶም ካረድ ሲያዘጋጅ የመጀመሪው ሸማች መሆናቸውን አውቃለሁ፡፡ በ 2012 ም፤ ለኢሳት የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅት ሲደረግ፤ ዋና አስተባባሪ እሳቸው ነበሩ፡፡ እንደውም አሁን እሳቸውን ከሚከሷቸው ሰዎች አንዳንዶቹ፤ በዚያን ግዜ በቤተክርስቲያናችን የአቶ መለስ ዜናዊ ሀዘን እንዳይደረግ መከልከል፤ የሰዎችን መብት መንካት ነው ብለው፤ ወንድም ሰለሞንን ሲያስቸግሩና ሲነተርኩ የነበሩ ሰዎች ናቸው፡፡

11- እጅግ በጣም የሚገርመው ደግሞ፤ ትናንት ከትናንት ወዲያ ዶ/ሩን ሻርለትን ወክለው በአትላንታና በዲሲ በሚደረጉ ዝግጅቶች ላይ ንግግር እንዲያደርጉ ሲገፋፉ የነበሩት ሰዎች፤ ዛሬ በውስጣቸው በተፈጠረ አለመግባባት ምክንያት፤ ዲባቶ ሰለሞንን የጠላት ወገን አድርጎ መሳል፤ ምን ያልህ ከራሳችንም የተጣላንና የፖለቲካ አስተሳሰባችን ሁሉ ቀሽም፤ አርባ አመትም ያላደገ እንደሆንን ያመለክታል፡፡ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች ካርባ አመት በሁዋላም ህልውናቸው በሌላ ስራ ስለማይገለጽ፤ በአካባቢያችን ተቆጣጥረነዋል የሚሏቸው ተቋማት፤ በሌሎች ከነሱ ባልሆኑ ወገኖች የተያዙ ሲመስላቸው፤ ያንን ለማስመለስና ህልውናቸው ይገለጽ ዘንድ ወደስም ማጥፋትና የፈጠራ ክስ ያዘነብላሉ፡፡ እዚህ ውስጥም እነዚህ ባለአርባዎቹ ሳይኖሩበት አይቀርም፡፡

12- ጎበዝ፤ ትንሽ እንብሰል፡፡ ትግላችንም፤ ትግል ካልነው ይብሰል፡፡ በቂና ግልጽ ጠላቶች ስላሉን፤ እንደሰለሞን አይነት ቀና ሰዎችን ጠላት ማድረግ፤ ወይም ጠላት ፍለጋ በባትሪ መውጣት አያስፈልገንም፡፡ እንዴት ያበሳጫል፤ በዚህ እነአንድነት ፍዳቸውን በሚያዩበት ሰዓት እንዲህ ያለውን ማስተባበያ እንድንጽፍ መገደዳችን፡፡

ተክለ (ሚካኤል)፤ ለአስተርዮ ማርያም፤ 2007/15፤ ቶሮንቶ፤ ካናዳ